

PRINTED BY
International & Public
Relations Directorate

FEB
2021

## Training and Consultancy Division holds workshop

Monthly Newsletter Vol 17 No. 6

# የኢትዮጵያ
# ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
# Ethiopian Civil Service University



# ECSU
## Officially Inaugurates Research Resource Center

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


ECSU Officially Research Resource Center Inaugurates — 1

RCS Holds Annual Consultation and Research Validation Workshop — 5

APD Provides Training to Students — 3

Training and Consultancy Division Hold Workshop — 7

CCITC Holds Workshop — 4

የምርምር አበልፅጎት ማዕከል — 9

RCS Holds Annual Consultation and Research Validation Workshop — 5

የአካዳሚክ ሰራተኞች መብትና ግዴታ — 10



**Editor In -Chife**
Tariku Ayano

**Editors**
Anteneh Demisse
Meley Tekeste

**Photos**
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

ግራፊክስ እና LAYOUT DESIGN
Dereje Tesfaye


## ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሙሉ

ውድ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በሙሉ አስተያየት፣ጥቆማ ፣ ጽሁፍ ወይም ማንኛውም አይነት መረጃ አለኝ የምትሉ በተቋሙ ድረ-ገጽ (ecsu.edu.et) በተዘጋጀው መላክያ ፎርም በኩል ስም ወይም ኢሜል አድራሻ መፃፍ ሳያፋልግ መላክ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

መገኛ አድራሻ፡- Quick Links

For Comments & Suggestions /ለአስተያየቶች እና ጥቆማዎች

Messages, Comments and Suggestions *

# የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

የኮቪድ 19 ቫይረስ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ መግባቱ ከተረጋገጠ እነሆ አንድ ዓመት ተቆጠረ፡፡ በዚህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥም በርካቶች በቫይረሱ ተይዘዋል፤ ውድ የሆነው የሰው ልጅ ሕይወትም አልፏል፡፡ ማህበረሰቡም ከወረርሽኙ ራሱን ለመከላከል በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አማካይነት ይተላለፍ የነበረው የጥንቃቄ መመሪያዎ በአግባቡ ሲተገብር ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በአንድ አሀዝ በሚለካበት ወቅት የነበረው ይህ ራስን ከቫይረሱ የመከላከል ጥረት የቫይረሱ ስርጭት ከጊዜ ወደጊዜ በከፍተኛና በአስደንጋጭ ሁኔታ እየጨመረ ባለበትና በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር በሶስትና በአራት አሀዝ በሚገለጽበት በአሁኑ ወቅት ላይ በእጅጉ ቸል መባሉና በማህበረሰባችን ላይ የሚታተው የመዘናጋት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ ይህ መዘናጋታችንም ውድ ዋጋን እያስከፈለን ነው፡፡ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከፍ ከማለት ባሻገር እየተቀጠፈ ያለው ውድ የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት በከፍተኛ ሁኔታ እያሻቀበ ይገኛል፡፡

በመሆኑም እኛም ነገ በቫይረሱ ላለመያዛችን ምንም ዋስትና የለንምና በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን እያሳየን ያለውን ቸልተኝነት በማስወገድ ለራሳችን ብሎም ለቤተሰቦቻችንና በአጠቃላይ ለማህበረሰባችን ስንል ራሳችንን ከቫይረሱ
እንጠብቅ የሚለውን መልዕክታችንን ደጋግመን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

**ዝግጅት ክፍሉ**

# ECSU Officially Inaugurates Research Resource Center

Ethiopian Civil Service University, Research and Community Service Division officially inaugurated the newly established Research Resource Center on January 28, 2021 at the presences of ECSU's top management, directors, researchers and invited guests.



On the inauguration program, Professor Fikre Dessalegn, Ethiopian Civil Service University President, congratulated the university community for the achievement in establishing the Research Resource Center. "In our previous assessment, we found that inadequate budget allocation, lack of clear research policies and guidelines, and the lack of a comprehensive research resource center were major hindrances to the research works. By the efforts exerted to solve these problems, 6 million birr has been approved for the research budget and project system has been developed to support the research works. Clear research policy and guide line have also been prepared. In addition, we have now set up this research resource center to strengthen our research works, and it has been officially inaugurated today", pro. Fikre said. He also noted that the center will be more organized within short period of time by including national and international information, software and other supporting materials beyond the E-resources. He urged the researchers and the academic staffs in general to use the center effectively and work harder and take ECSU to a higher level.



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*



**Dr. Alemayehu Debebe**
*Vice President of Research and Community Service*

Dr. Alemayehu Debebe, Vice President of Research and Community Service, on his part welcomed the participants in the program and thanked all individuals contributed in the establishment of the centre for their effort for the realization of the center. He also said that it is very important to do and publish continuous research works in the academic world. The launch of this resource center is a step forward in our research and plays a significant role in making our university more visible in the international world and upgrade our status. The center has been organized properly with a large electronic resource that researchers, teachers and students in the university compound can access these resources easily, Dr. Alemayehu added.

He also explained that the resource center has 31 subscribed e-journal databases, 55,000 e-books, more than 1,500 e-thesis and dissertations and 6 international online database access connected with ECSU server, and can be access using the local network.










# APD PROVIDES TRAINING TO STUDENTS



**Dr. Temesgen Birega**
*Director for the Academic Program Directorate*



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*

Ethiopian Civil Service University Academic Program Directorate organized training for the 2020/21 academic year students from December 23- 25, 2020 at Abay Hall. The training focused on COVID -19 Directives and Creating psychological readiness to re-start the face to face teaching learning program.

At the program the university's different directorates including Library and Documentation Directorate, Guidance and Counselling Directorate and Students Service Directorate have briefed the rules and regulations of their respective directorates and requested the students to respect the general rules of the university.



At the opening of the training, Dr Temesgen Birega, Director for the Academic Program Directorate, Said this training will help the students to gain clear information about what is expected from the students during the COVID-19 epidemic. It also creates psychological readiness for the students to continue their lesson effectively in the first academic semester. Besides, it helps students to know each other and share their experience and background and create conducive teaching learning environment while they staying in the university compound he underscored.



A directive prepared by Ministry of Science and Higher Education will be used as a guideline for the teaching and learning efforts in educational and training institutions during the COVID-19 pandemic with the necessary care until a reliable COVID-19 vaccine or treatment is available and ensure the opening of the institutions in accordance with the guidelines set by the Ministry of Health.

# CCITC Holds Workshop

Ethiopian Civil Service University Center for Cross-Cutting Issues Training and Consultancy (CCITC) held national workshop on Contemporary Challenges of Youth in Ethiopia and the Way Forward on January 26, 2020 at the Hidasie Hall . On the workshop concerned personalities from Federal, Regional and Cities Administrations participated.



**W/ro Seble Mulugeta**

*Director, Center for Cross-cutting Issues Training and Consultancy*

On the opening of the workshop Dr. Waqgari Negari, Vice President for Training and Consultancy Service Division, welcomed the participants and explained the importance of working together with the youth and paving the way for them to participate in different national and social activities. In his motivational speech delivered to the participants, he emphasized the significant of extensive effort on youth empowerment in all areas and give a due attention to youth-based development programs to produce lasting outcome for the overall development of the country in general.

On the workshop, two research papers entitled "Factors Motivating and Hindering Youth Participation in Youth Development Programs in Ethiopia" and "Contemporary Challenge of Youth in Ethiopia" were presented by Dr. Abebe Assefa and W/ro. Kumneger Fikre respectively.

In their presentations, the presenters indicated that the youth has great potential and ideas that can make a big difference. However, they are facing many challenges that hinder their participation in different activities. According to the presenters- unemployment, irregular migration, quality of higher education, substance abuse, social media abuse and harmful traditional practices are the major challenges that youths are facing in the contemporary situation.



**Dr. Waqgari Negari**

*Vice President for Training and Consultancy Services*

In addition, they also recommended the need to give priories to design program activities that meet youth personal goals and encourage family involvement in youth development program as well as healthy youth relationships.

Participants on their part expressed their appreciations for ECSU for organizing the workshop and discussed on a number of issues related to the challenges of the youth and the way it is being considered based on the experiences from their respective institutions. They also forwarded ides that need to be incorporated in the youth development programs.





# RCS Holds Annual Consultation and Research Validation Workshop

Ethiopian Civil Service University Research and Community Service Division held two days annual stakeholders consultation and research validation workshop from 13 to 14, January 2021 at Abay Hall.

The major objectives of this workshop are to identify thematic areas for problem solving research by discussing with stakeholders, sharing ideas on the research undertaken and strengthening the relationship and working together with the stakeholders and representatives from both federal and regional institutions and city administrations participated on the workshop.

In his opening address, Dr. Alemayehu Debebe, Vice President for Research and Community Services, welcomed the participants and said that ECSU has prepared ten year strategic plan. In line with this and with new vision, Research and Community Service Division has also prepared the team for further enhancement in research



and community services in the next ten years. It has established a research resource center and is building its capacity from different aspects. In addition, it is disseminating the researches undertaken so far by using journals to the public. Currently, fifty seven research works are being done by the university scholars and researchers in different thematic areas, Dr. Alemayehu added.

He also called up on the participants to exert their at most efforts to put into practice the research done in their respective institutions and expressed ECSU'S readiness to work in collaboration with them by exchanging information and providing professional supports.



**Dr. Alemayehu Debebe**
*Vice President of Research and Community Service*







On the workshop seven research papers were presented and participants discussed and forwarded their comments and suggestions on the paper presented by the researchers. They also proposed some research thematic areas that they need to be studied in the future. In this regard, problems related with the implementation of JEG, the practical needs of the country and the areas that the students are being graduated from public universities, employees' occupational health and safety, migration, problem in both urban and rural land management, human resource development and human resource mobilization, the effectiveness of researches undertaken etc. were proposed by the participants as a research thematic areas.





On the program, Dr. Mekonnen Kassahun and Dr. Mulugeta Worku Director for Center for Public Sector Reform Studies and Center for Ethics and Integrity respectively briefed the participants the roles and responsibilities of their respective centers and the challenges they are facing in their research works. They also called upon the participants to further strengthen their relations with the centers and work together to achieve their common goal.





# Training and Consultancy Division hold workshop

Ethiopian Civil Service University Training and Consultancy Division held consultation workshop with stakeholders on “The Consultancy Service Provision Practices” on January 25, 2021 at Hidasse Hall. On the workshop different stakeholders from Federal, Regional and Cities Administrations participated.




**Dr. Waqgari Negari**
*Vice President for Training and Consultancy Services*



**Ato Daba Moti**
*Director, Consultancy Coordination Directorate*

In his opening speech, Dr. Waqgari Negari, Vice President for Training and Consultancy Services, welcomed the participants and expressed ECSU’s readiness for further collaboration with stakeholders. He also noted that over the past 25 years, a lot of work has been done by ECSU in education, training and consulting services. Now it is time to get out of the traditional way of doing things and reorient our systems of training and consultancy service provision practices. Based on this, this workshop is organized to discuss how can we collaborate with the stakeholders and work in an integrated way and effectively carry out our consulting work in the future, Dr. Waqgari added.

On the workshop a brief explanation on consultancy service provision practices by both government and ECSU since 1994E.C and a Case Study on Urban Structural Planning (USP) and the way forward were presented by Ato Gebretinsay Tesfay and Ato Zeleke Lerango respectively.

Participants on their part expressed their appreciations for the workshop organizers and discussed on issues raised by the presenters .Besides, they forwarded ides which they think for further strengthening the consultancy services in an integrated manner.  They also indicated that the importance of multidisciplinary approaches in conducting national projects, involving an indigenous knowledge and integration of both private and public sectors for the overall achievements of the intended goals in the consultancy services.





# የምርምር አበልጽጎት ማዕከል

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምር ስራዎችን በማካሄድ እንዲሁም የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በመስጠት በዩኒቨርሲቲው የፐብሊክ ሴክተሩን አቅም ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት የመደገፍ ተልዕኮን በማንገብ ለተልዕኮውም ስኬት በስፋት በመስራት ላይ የሚገኝ ዘርፍ ነው። ዘርፉ በእካሁኑ ጉዞውም የፐብሊክ ሴክተሩን አገልግሎትን ለማሻሻል እና የአመራሮችን እና ባለሙያዎችን አቅም ለማጎልበት ከፍተኛ የሆነ ሚና ያላቸውን ችግር ፈቺ ምርምሮችን አካሂዷል፤ እያካሄደም ይገኛል ። ዘርፉ በስሩ ባዋቀራቸው ሁለት የምርምር ማዕከላት የሥነ ምግባርና ምሉዕ ሰብዕና ምርምር ማዕከል እና የፐብሊክ ሰርቪስ ሪፎርም ምርምር ማዕከል አማካይነትም በህዝባዊ አገልግሎት አቅም ግንባታ እሴት የመጨመሩን ሂደት በይበልጥ እያፋጠነና ከዕለት ዕለት ተጨባጭ የሆነ ጉልህ አስተዋጽኦውን እያበረከተ ይገኛል። የተለያዩ የምርምር ምክረሀሳቦችን በመቀበል፤ በተሰሩ የምርምር ስራዎችም ላይ የተለያዩ የአስተችቶት አውደ ጥናቶችን በማካሄድና ግብዐት የሚሆኑ ሀሳቦችን በመውሰድና በምርምሮቹ የተገኙ ውጤቶችን የበለጠ በማጠናከር እንዲሁም ስራቸው የተጠናቀቁት ምርምሮችን በማሳተም ለሚመለከታቸው ተቋማት ተደራሽ እንዲሆን አድርጓል። ከዚህም ባሻገር በዩኒቨርሲቲው ምሁራን አማካይነት የሚሰሩ የምርምር ስራዎችንም በመደገፍ ተቋማዊ የምርምር ስራዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ በማድረግ ላይ የሚገኝ ዘርፍ ነው።



ዘርፉ የምርምር ስራዎችን በተጠናከረ ሁኔታና በቅልጥፍና ለማከናወን ያስችለው ዘንድ፤ ተመራማሪዎችም ለምርምር ስራዎቻቸው የሚሆኑ ግብዐቶችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት የተደራጀ የምርምር አበልጽጎት ማዕከል በማቋቋም ማዕከሉን የዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮች ፣ ዳይሬክተሮች ፣ ተመራማሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ጥር 19 ቀን 2013 በይፋ አስመርቋል ።

በምረቃ ፕሮግራሙ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለመላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የምርምር አበልጽጎት ማዕከሉን ለማቋቋም በተደረገው ጥረት ውስጥ ላበረከተው አስተዋጽኦ አመስግነው የማዕከሉ መመስረት በዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ የምርምር ስራ ላይ የሚኖረውን ጉልህ ሚና አብራርተዋል። ዩኒቨርሲቲውም ከዚህ በፊት ባደረግነው ግምገማ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ስራዎችን የሚገዳደሩ አንዳንድ ጉዳዮች ተነቅሰው የተለዩ መሆናቸውን ያስታወሱት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ለአብነት ያህልም ለምርምር የሚመደበው በጀት በቂ አለመሆን ፣ ግልጽ የሆኑ የምርምር ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ፕሮቶኮሎች አለመኖራቸው እንዲሁም የተሟላ የምርምር አበልጽጎት ማዕከል አለመኖሩ ለምርምር ሥራዎች ዋነኛ ችግሮች መሆናቸውን እንደተረጋገጠና እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍም ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ተናግረዋል። በዚህም መሰረት በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በተደረገው ጥረት በዚህ ዓመት ለምርምር ስራ የሚውል በቀረበው ፕሮፖዛል መሰረት ስድስት ሚሊዮን ብር በጀት የተመደበና ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የምርምር ሥራዎችን የሚደግፍ የፕሮጀክት ሥርዓትም ተዘርግቷል። የምርምር ስራዎች የሚስተናገዱባቸው ግልፅ የሆኑ የምርምር ፖሊሲና መመሪያዎችም ተዘጋጅተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ፕሮፌሰር ፍቅር በመልዕክታቸው የምርምር ሥራዎችን ለማጠናከርና ተመራማሪዎች ለምርምራቸው ግብዐት የሚሆኑ መረጃዎችን በአንድ ቦታ ሆነው በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ ለማስቻል የምርምር አበልጽጎት ማዕከሉ ቀደም ሲል የነበረውን ችግር የሚቀርፍ ከመሆኑ በላይ የምርምር ስራውን በመደገፍ ሂደት ላይ ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ እንደሚኖረው በመጠቆም ማዕከሉ በይፋ ተከፍቶ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑን አብስረው ማዕከሉ ወደፊትም ከኤሌክትሮኒክስ መረጃዎች ባሻገር ሰፋፊ አገራዊና ዓለም አቀፍ መረጃዎችን እንዲይዝ በማድረግና የተለያዩ አጋዥ ሶፍትዌሮችንና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶችን በማካተት፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይበልጥ የተደራጀና ታላቅ ማዕከል








ለማድረግ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጠንክሮ የሚሰራ መሆኑን ገልጸው ተመራማሪዎችም ጠንክረው በመስራት ራሳቸውን እና ተቋሙን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ማዕከሉን በብቃት እንዲጠቀሙ አሳስበዋል፡፡

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝደንት ዶ/ር አለማየሁ ደበበ በበኩላቸው ማዕከሉ እውን እንዲሆን ላደረጉት ጥረት ማዕከሉ እንዲቋቋም አስተዋጽኦ ያደረጉትን የስራ ክፍሎችንና ግለሰቦች በሙሉ አመስግነው ማዕከሉ እዚህ ደረጃ ላይ ለማድረስ በተደረገው ጥረት የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች መካከል ትልቅ መስተጋብር የተፈጠረበት፤ በቅንጅት የመስራት መንፈስ በእጅጉ ጎልቶ የታየበት እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ከፍተኛው አመራሩም በሁሉም ረገድ ከፍተኛ የሆነ እገዛ እያደረገና በየወቅቱም የነበረውን ሁኔታ ሲከታተል መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡ የዚህ ማዕከል መመስረት በራሱ አንድ እርምጃ እንጂ ግብ አይሆንም ያሉት ዶ/ር አለማየሁ ትልቁ ግባችን ዩኒቨርሲቲ ያለምርምር ስራ ምንም አይደለምና በምርምር ስራ ራሳችንን አልቀን በአለም አቀፍ ደረጃ የዩኒቨርሲቲ ደረጃዎች የሚሰጥበት አንዱ መስፈርት የምርምር ስራ በመሆኑ በዚህ ረገድም በምንሰራቸው የምርምር ስራዎች የምርምር ግብዓት በማሟላት በምርምር ስራዎች ለዓለም አቀፍ ደረጃ ልቀን ለመታየት ተግተን መስራት ይኖርብናል፤ ዩኒቨርሲቲውም ለምርምር ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ ዶ/ር አለማየሁ ገለጻም ዩኒቨርሲቲው በ2013 ዓ.ም ብቻ አምሳ ስድስት የምርምር ፕሮጀክቶችን መርምሮ በመቀበል እና በገንዘብ በመደገፍ አርባ ሰባቱን ወደ ስራ ለማስገባት የተቻለ ሲሆን እነዚህ የምርምር ስራዎች ተጠናቀው ሲታተሙ ተቋሙ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖረውን ስፍራ ከፍ በማድረግ ሂደቱ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የማዕከሉ መከፈትም ተመራማሪዎች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ፤ ማዕከሉን በመጠቀም የተሻለ የምርምር ሀሳብ በማምጣት እና የተሻለ የምርምር ውጤት በማስመዝገብ ራሳቸውንም ሆነ ተቋሙን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚደረገውን ጉዞ በእጅጉ የሚያሳልጥ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡

በአበልጽጎት ማዕከሉም በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ተመራማሪዎች፣ መምህራንና ተማሪዎች 31 ኢ-ጆርናሎት ዳታ ቤዞች (E-Journals 31 Databases)፣ 55 ሺህ ኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍትን (55000 E-Books) ፣ 1500 ኢቴሲስና ዲሰርቴሽኖችን (1,500 E-Thesis and Dissertation)፣ እንዲሁም 6 ኦን ላይን ዳታ ቤዝዎችን (6 Online Database ) በቀላሉ ማግኘት በሚችሉበት ሁኔታ በአግባቡ መደራጀታቸውንም በማዕከሉ የምረቃ ሥነሥርዓት ወቅት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም በማዕከሉ ለተለያዩ ጉዳዮች የሚያገለግሉ ኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን በየፈርጃቸው የቀረቡ ሲሆን በዚህም መሰረት በማዕከሉ :-

በ (JSTOR ) የላይ ለተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት እና ለምርምር ሥነ ዘዴ ጉዳዮች በቀላሉ በግብዐትነት የሚያገለግሉና በ 75 የትምህርት ዓይነቶች ላይ የተዘጋጁ ከ 12 ሚሊዮን በላይ የአካዳሚክ መጽሔት መጣጥፎች ፣ መጻሕፍት እና የመጀመሪያ የመረጃ ምንጮች primary sources ፤

በ African Journals Online (AJOL) ላይም ከ 31 የአፍሪካ አገራት የተሰበሰቡ ከ 500000 በላይ ጆርናሎች ፣ የመጽሐፍ ምዕራፍ ፣ አጠቃሎዎች (abstracts) ፤

በ Science Direct ከ 18 ሚሊዮን በላይ ይዘቶች ያላቸው ከ 4,000 በላይ የትምህርት መጽሔቶች እና ከ 30,000 ኢ-መጽሐፍት ፤

ከ Eerald E-Journal Collection በንግድ ፣ በማኔጅመንት ፣ በኢኮኖሚክስ ፣ በኢንጂነሪንግ ፣ በኮምፒዩተር እና በሌሎች ማህበራዊ ሳይንስ መስኮች ላይ የተዘጋጁ ከ 255,000 በላይ መጣጥፎች በማዕከሉ እንዲገኙ ተደርጓል።

ከዚህም ባሻገር በማዕከሉ በ University of Chicago Press እና በ Oxford University Press ላይ የተለያዩ መጻህፍትና የምርምር ግብዐቶችን ማግኘት የሚቻል ሲሆን ወደፊትም ከእነዚህ እና ሌሎች የኤሎክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮች የምርምር ሪሶርሶችን በማካተት፤ ከሀገር ውስጥም የብሔራዊ ባንክን፣ የማዕከላዊ ስታትስቲክ ባለስልጣንን ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ወዘተ. የመሳሰሉትን ተቋማትን መረጃ በማዕከሉ እንዲካተት የማድረግና ማዕከሉ በማስፋፋት ስራ የሚሰራ መሆኑም በምርቃት ስነ ስርዓቱ ላይ ተገልጿል።

እነዚህን መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ መጣጥፎችና ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በሚከተሉት አድራሻ ማግኘት ይቻላል

**ECSU Digital Library URL**

**diglib.ecsu.edu.et**

**or**

**http://10.2.0.14**

**Electronic Journals URL**

**http://www.ecsu.edu.et/electronic-journal**

**OPAC URL**

**http://10.2.0.12**












# የአካዳሚክ ሰራተኞች መብትና ግዴታ

## የአካዳሚክ ሰራተኞች መብት

### ማንኛውም ተቋም አካዳሚክ ሰራተኛ፡-

ሀ) በሀገሪቱ ህግ፣ በተቋሙ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ስርዓት መሰረት የማስተማር፣ በምርምር እና በማ ህበረሰብ አገልግሎት ተግባር ላይ በነፃነት የመሳተፍ፤

ለ) ሚኒስተሩ በሚያወጣው መመሪያ፣ በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መሰረት የሰባቲካል እረፍት የማግኘት፣ ሚያውን የሚዳብር ትምህርትና ሥልጠናን የማግኘት እና የአካዳሚክ የሙያ እድገ ትን የማግኘት፤

ሐ) ግልጽና ፍትሃዊ አስተዳደር የማግኘትና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው መሰረት በመንግስት የሚወሰን ወይም በግል ተቋሙ አቅም ላይ የተመሰ ረተ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት፤

መ) በተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ እቅድና የውስጥ ደንብና መመሪያዎች ዝግጅትና የሥርዓተ ትምህርት ሂደት አግባብነትና ጥራት ላይ አስተያየት የማቅረብ፤

ሠ) የግል ማህደሩን የማየትና የመረጃዎችን ግልባጭ የማግኘት፣ የስራ አፈጻጸም ግምገማ ሂደቱ ላይ የመ ሳተፍና ውጤቱን የማወቅ፣ እንዲሁም በማህደሩ ውስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች ለተቋሙ አስተዳደ ራዊ ጉዳይ ወይም አግባብ ባለው ህግ በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር በሚስጢር የመጠበቅ፤

ረ) በተቋሙ ግቢ ውስጥ የራሱና የግል ንብረቱ ደህን ነት ተጠብቆ ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት፤

ሰ) ስለተቋሙ ዕቅድ፣ እድገት፣ የትኩረት አቅጣጫ ሁኔታና የክንውን ውጤቶች መረጃ የማግኘት፤

ሸ) አካዳሚክ ሰራተኛን መምረጥ ተገቢ በሆነበት ሁሉ የመመረጥና የመምረጥ፤

ቀ) በዲሲፕሊን ክስ ጉዳይ ክሱን የማወቅ፣ማስረጃ የማቅረብ፣ የመስማት፣ የውሳኔ ግልባጭ የማግኘት፣ ይግባኝ የመጠየቅ እና ፍትህን የማግኘት መብት አለው።

ምንጭ፡- የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 ዓ.ም

## የአካዳሚክ ሰራተኞች ግዴታ

### ማንኛውም ተቋም አካዳሚክ ሰራተኛ፡-

ሀ) በሀገሪቱ ህግ፣ በተቋሙ ተልዕኮ፣ እሴቶች እና ስርዓት መሰረት የማስተማር፣ምርምር የማድረግ እና የማህበረ ሰብ አገልግሎት የመስጠት።

ለ) በራሱ የሙያ መስክና ብቃት መሰረት ለሀገር ተቃሚ የሆነ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምርን የማካሄድና ዕውቀትና ክህሎትን የማሸጋገር የሚያስተምረውን ትምህርት በጥና ትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የማድረግና በየግዜው የማ ሻሻል፤

ሐ) ሥርዓተ ትምህርትን በመገምገምና በማጎልበት ሂደት ላይ ተገቢውን ሚና የመጫወት፣እንዲሁም በስርዓተ ትምህርቱ አተገባበር ላይ ኃላፊነቱን የመወጣት፣

መ) ተማሪዎች የተቋሙን ተልዕኮ መሪ እሴቶችና የከፍ ተኛ ትምህርት አላማዎችን እንዲያውቁ የማገዝና የመርዳ ት፣ተማሪዎችን የመመዘን እና ተገቢውን ውጤት የመስ ጠት፣የተማሪዎችን ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን የማስተ ናገድና በአጠቃላይ የሚጠበቅበትን ሙያዊ ስነ-ምግባር የመወጣት፤

ሠ) የከፍተኛ ትምህርት አላማዎችንና ተቋሙ የሚመራበ ቸውን እሴቶች የማክበር፣የመተግበርና አካዳሚክ ነፃነትን በሙያዊ ስነ-ምግባርና አግባብነት ባላቸው የዚሁ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት የመጠቀም፤

ረ) ልዩ ፍላጎት የሚሹ ተማሪዎችን የመደገፍና የማብ ቃት፣

ሰ) ሙሉ የስራ ጊዜውን ለተቋሙ የማዋል፤

ሸ) በመማር ማስተማር ሂደት የራሱን ፖለቲካዊ አመለ ካከት ወይም ሀይማኖት በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ከመጫን የመቆጠብ፤

ቀ) ከተቋሙ ማህበረሰብ አባላት በሚኖረው ግንኙነት በህገ-መንግስቱ የተረጋገጡ መብቶችን ከሚጻረሩ ድርጊ ቶችና አሰራሮች የመቆጠብ፤

በ) በተቋሙ የመቋቋሚያ ህግ ወይም መመስረቻ ሰነድ እና የተቋሙ የሴኔት ደንብ መሰረት የሚሰጡት ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፤

ተ) ከሌላ ተቋም ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ስምምነት መሰረት የአካዳሚክ ሰራተኞችን በጋራ ስለመቅጠር በዚህ አዋጅ ስለመቅጠር በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሙሉ ሀይሉን የስራ ጊዜውንና ትኩረቱን ለተቋሙ የማዋል ግዴታ አለበት።

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**

Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016

P.O.Box5648, E-mail: www.lprd @ecsu.edu.et ,

Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz

Facebook: Ethiopian Civil Service University





BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995


**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*